## የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ አስማውና አስፈሳጊነቱ

መልካም አስተዳደር ለማስፈን ፤ዲሞክራሲ ስርአት ለመገንባት እንዲሁም ቀጣይነት ፤ዘላቂነት ያለው ኢኮኖሞያዊ እድገት እና ልማትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ሲቪል ሰርቪሱ ቁልፍሚና በመጫወት የተገልጋይን ማህበረሰብ ፍላጎት እንዲያረካ ማስቻል ሲሆን ህብ/ሰቡ የሚፈልገውን ፍላጎት በግዜና በጥራት የሚፈጸምለት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የመንግስት ተቋማት ማግኘት መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑና አገልግሎት ፈሳጊ ህ/ሰቡን ከደረሰበት ማህበራዊ ንቃትን በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ወስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ከሚፈስገው ቅልጥፍና ጋር የሚራነድ መንግስታዊ አደረጃጀት መኖር የግድ ነው፡፡ በአጠቃሳይ መንግስታዊ አገልግሎት የሚፈስገውን ህዝብ ፍሳጎት እያደገ በመምጣቱ በአለም አቀፍ ደረጃ እያደገ እየጠነከረ የመጣውን አለም በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ወስጥ መገኘቷ ከነዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች ጋር የሚማማ መንግስታዊ ተቋማት አሰራር መፍጠር በሚያስፈልግ ነባራዊ ሁኔታ ሳይ እንገኛለን፡፤

### መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጽንሰ ሃሳብ

አንድ ተቋም ሁለንተናዊ የስራ ፍሰት በመዳሰስ ሃሳቀር የሆነ አሰራር አስወግዶ ስርነቀል በሆነ መልኩ አሰራርን ለውጦ ተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት በአነስተኛ ወጪ ፤በአጭርግዜ፤ጥራት ያለው እንዲሆን በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ ማምጣትና የተቋሙን አፈጻጸም ለማድረግ የሚያስችል የለውጥ አይነት ነው፡፡

በመሰረታዊ አስተሳስብ ለውጥ እና ስር ነቀል የአሰራር ለውጥ ሳይ የተመሰረተ እምርታዊ የአፈጻጻም ውጤት የሚያስገኝ እና አዲ የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት የሚያስችል የለውጥ አይነት ሲሆ ሃሳቡ ማብሪረያ ውስጥ አራት ገዢ ሀረጎች

1.መሰረታዊ የአስተሳስብ ለውጥ

2. ስር ነቀል

3.አምርታዊ የአፈጻጸም ውጤት

4.የሥራ ሂደት

## መሰረታዊ የአስተሳስብ ለውጥ

የለውጥ ስራ የሚጀምረው መሰረታዊ የሆነ አስፈላጊነት ወይም የህይወት ጥያቄ ማንሳት ነው ይህውም፡-

ይህ ሴክተር በአሁኑ ግዜ ያስፈልጋል ወይ ? መኖር አስፈላጊ ከሆነ መኖር ያለበትን አሁን ባለው መልኩ ነው ለመኖሩ መሰረት የሆነውን ስራ እየሠራ ባለው ሁኔታ የሚሰራው ለምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ የግድ ይሳል፡፤ በመሆኑንም አሁን ያለውን አስተሳሰብ መናድ ወይም መገልበጥ እንዲቻል ተገንዝቦ የሚነሳ መሆኑን ከዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

## ስር ነቀል ለውጥ Radical change

ለውጡ እንደመጣ የሚገለገው ከላይ እንደተገለጸው ነገሩን በመቀባባት ወይም ቀለም በመቀባት ለማሻሻል ሳይሆን ነባሩን እንደነባር በመቁጠር ከባድ ወረቀት መጀመር ነው፡፡

1.ምንም ታሳቢ አርጎ አይነሳም

2. ህጎችና መመሪያዎችን መሰረት አያደርግም

3. የሥራ ሂደቱን እንደገና ከስር መሰረቱ የመፍጠር ስራ ነው

4. ከማሻሻል ከመጠገን ከማጠናከር ወይም ከማደስ ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡

## አምርታዊ የአፈጻጸም ውጤት /Dramatic

እስካሁን ካሉ ልምዶች መረዳት እንሚቻለው ከለውጡ በሃላ የሚገኘው የአፈጻጸም ውጤት ተቀባይነት ባገኙት ዘመናዊ የአፈጻጸምመስኪያዎች ሲመዘን አምርታዊ የአፈጻጸም ውጤት የሚታይበት ነው፡፡

## የሥራ ሂደት





የስራ ሂደት ማለት ከግብአት አስከ ውጤት/ from in put to out put/ ለተገልጋዩ ህ/ሰብ እሴት በመጨመር ሙሉ አገልግሎት ለመስጠት የሚሰሩ ተያያዥነትና ተመጋጋቢነት ያላቸውን ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፧ የለውጡ ትኩረት ማዕከል እና የለውጡ ስራ የሚያውጠነጥነው::

## የለውጥ መንስኤዎች

በአሁኑ ወቅት አለም ከደረሰችበት የእድገት ደረጃና ከህ/ሰብ የእለት ተእለት ፍላጎት መጨመር አንጻር መሰረታዊ ለውጥ በማስፈለጉ በተናጥልም ሆነ በጋራ ተጣምረው  የለውጥ መንሰኤ የመሆኑ ሶስት አበይ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን አነሱም

1. ተገልጋይ/ Customer/
2. ውድድር/ competition/
3. ለውጥ/ change/

## መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ለምን አስፈለገ ?

ተቋማት አዲስ የስራ ሂደት ለውጥ /ፈጣን ምላሽ ሰጭነት/ ብቃትና ተገልጋይ ተኮር አሰራር እንዲኖራቸው ይፈስጋል፡፧

መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ከአዲሱ አለም ጋር ለመራመድ የሚያስችል ምርጥ የለውጥ መሳሪያ ነው::

በአለም ተጨባጭ ሁኔታ ወስጥ ውጤታማ ተቋም ሆኖ ለመዝለቅ ጥገናዊ ለውጥ ወይም  ማሻሻያ ብቻ በቂ አይደለም::

## በአዲሱ የመሰረታዊ  ስራ ሂደት ለውጥ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተገልጋይ ተኮር  አመለካካት እና እሴት ያላቸው ተቋማት እና ሰራተኞች

ከስራ ክፍል ወደ ስራ ሂደት ተኮር የስራ አደረጃጀት የተለወጡ መ/ቤቶች

በአፈጻጻም ምዘና ላይ ብቻ ሳይሆን በችሎታ ላይ የተመሰረተ

የሰው ሃይል አመራር ስርአት የተዘረጉ መ/ቤቶች

ከተቆጣጣሪነት ወደ አቅም ገንቢነት የተለወጡ መሪዎች የስራ ሃላፊዎች እንገኛለን:::

## ባለንስድ ስኮር ካርድ እንደ አፈጻጻም አመራር ስርአት

ያለንበት ዘመን የኢንፎርሜሽን ዘመን በመሆኑ በኢንዱስትሪው አብዎት ዘመን ከነበረው በተለየ ሁኔታ የመንግስት ሆነ የግል ተቋማት በርካታ ወስብስብ ችግሮች ተገርተውባቸዋል ፡፧ፈጣን ለውጥ ፧ተለዋዋጭ የደንበኞች ፍላጎት እንዲሁም ምህረት የለሽ ውድድር ዋነኛዎቹ ፈተናዎች ናቸው፡፡

### <<አዲሱ የሥራ አለም ስርነቀል የአስተሳሰብ ለውጥ የሚጠይቅ ነው>>

በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ወስጥ ማፍ የሚቻለው ብቁ ተወዳዳሪና ተመራጭ አገልግሎት ሰጭ ሆኖ በመገኘት ብቻ ነው፡፡

ብቁ ተወዳዳሪነት ሲጎናጽፍ የሚችሉ ወሳኝ መፍትዎች እንዳሉ ይታመናል፡፡ከዚህ መካከል ቁሳዊ እእምሮአዊ ሀብትን በአግባቡ አቀናጅቶ በመጠቀም የደንበኞችን/ዚጎችን/ፍላጎት የሚያረኩ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በጥራት /በፍጥነትና በተመጣጣኝ ዋጋና ማቅረብ ዋናኞቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማቅረብ ተቋማት የተለያዩ የለውጥ እርምጃዎችን ሲወሰዱ መቆየጣቸው የተስተዋለ ሲሆኑ በአገራችንም የተለያዩ የለውጥ ጥራቶች ሲደረጉ ቆይተዋል ፡፧በክልላችን ሆኖም በልዩወረዳችን በመንግስት ተቋማት በቅርቡ ተግባራዊ የተደረገው መሰረታዊ አሰራር ስርአት ለውጥ መንግስት የዜጎችን ፍላጎት ለሚሟላት ለለውጥ ግፊቶችን አውንታዊ ምላሽ ለመስጠትእና ከወቅቱ ጋር በእኩል ፍጥነት ለመጓዝ ከቀየሳቸው ፕሮግራሞች መካከል ዋነኛ ሲሆን የተቋማትን አፈጻጻም እምርታዊ በሆነ መልኩ ያሻሻላል ተብሎ የሚታመን ነው፡፡



lkg

# የፎቶ ገጽታዎች





እና አቅም ግንባታም በዚህ ያሉ ክፍተቶችን ድጋፍ በማድረግ መለየት መቻል አለበት እና እዚህ ነገር ላይ ሁላችንም ያሉ ችግሮችን እያስተካከልን አመራሩም ሆነ ባለሞያው የአገልጋይነት ስሜት ተላብሶ መስራት መቻል አለበት በሚል የውይይት ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን አስታውቀዋል፡፡

ሁሉም የፍትህ አካላት ተቀናጅተው እና በየሴክተራቸው ያሉ ክፍተቶችን በመለየት በየግዜው ተገናኝተን ብንሰራ የፍትህ ስርአት ማሻሻያውንም የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙን ሆነ

የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እና የህዝቡ የፍትህ ጥየቄ መልስ መስጠት እና ለውጥ ማምጣት እንችላለን፡፡በዚህ መሰረት ሳምንቱን መልካም አስተዳደር መርሆችን በመገንዘብ በያለንበት ቦታ የተጣለብንን የህዝብ ሃላፊነትም ሆነ አገልጋይነት ለህዝቡ በሚገባ ልናገለግለው እና ለጠየቀን ጥያቄ ፈጣን ምላሽ መስጠት መቻል አለብን፡፡

በመጨረሻም የልዩ ወረዳው አስተዳዳር እንዳሉት ዛሬ የጠዘጋጀው ውይይት ያሉብንን ችግሮች በማየት በቀጣይ ለመታረም እና ለማስተካከል ሰለሆነ በቀጣይ እያስተካከልን መሄድ ይጠበቅብናል፡፤እነዚህን ዛሬ የተወያየንባቸውን በተለይ የኮሚኒቲፖሊሲንግ ከተጠናከረ ህ/ሰቡን ስለወንጀል አስከፊነት አስተማሪ ነው ወንጀል ከመሰራት ይቆጠባል፡በዚ መሰረት ወንጀል ከመፈጠሩ በፊት መከላከሉ ላይ ፖሊስ ከህዝቡ ጋር በመሆን የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ስራ አጠናክሮ በመስራት ለውጥ ማምጣቱ መቻል አለበት፡





የዚህ ለውጥ ሂደት የአሰራር ሂደት ቀጣይነት ለማረጋገጥ አፈጻጸምን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል የአፈጻጸም አመራር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ቀድሞ ሲል በአገራችን ተግባራዊ ሲደረግ የቆየው ውጤት ተኮር እቅድ አፈጻጸም ምዘና ስርአት የተቋማትን የትራንስፎርሜሽ ጥራት ይደግፋል ተብሎ የተነደፉ ቢሂሁንም በነባር የባህል አስተሳሰብ ፤የአመለካካት ፤ቴክኒካዊ እንዲሁም በእውቀትና ክህሎት ክፍተት ችግሮች ምክንያት በሚጠበቀው መልክ ተግባራዊ ሲደረግ አልቻለም፡፡

ሰለሆነም በአገራችን በአሁኑ ግዜ በመካሄድ ላይ ያለውን የለውጥ (ትርንስፎርሜሽን) እና የተሃድሶ ጥራት በክልላዊ ራእይ፤ከተቋማት ተልኮና ስትራቴጂ ጋራ አስተሳስሮ ተያያዥነት ባለው መልክ ለመምራት የውጤት ተኮር ስርአቱን በሚዛናዊ ስኮር ካርድ ቅኝት መቅረጽ አስፈላጊ ሆነዋል፡፡

## ባላንስድ ስኮርድ ምንድ ነው

ባልንስድ ስኮር ካርድ በሚመለከት ኖርተን እና ከፕላን /1996 / የተሰኙ ጹሁፍነት እንደሚከተለው ተርግመውታል ፡፡ባልንስድ ሶኮር ካርድ ተቀማዊ ራእይና ስትራቴጂ ግልጽና የተብራራ እንዲሆን የሚያደርግ ፤እንዲሳኩ ፤ከታቀዱ ተቀማዊ አላማዎች / Targets/ በመነሳት

አፈጻጻምን ከስትራቴጂያዊ እቅድ ጋር የሚያስተሳስሩ የእይታ መስኮችን / Perspectives/ ለይቶ በማውጣት አፈጻጻምን የእይታዎች አኳያ እንዲላክ ለማድረግ፤እንዲሁም የስትራቴጂያዊ ግቦችን ስኬት ለመለካት የሚያስችሉ ተስማሚ መለኪያዎችን ለይቶ ለማስቀመጥና በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያገለግል የስትራቴጂያዊ የሥራ አፈጻጸም አመራር መሳም ነው፡፡

ባሳንስድ ሶኮር ካርድ አፈጻጸም ከስትራቴጂያዊ እቅድ ጋር እንዲተሳሰፍ የሚያደርግባቸው እይታዎች አራት ናቸው፡፡

የተገልጋይ እይታ ( Customer Perspective/ በዚህ እይታ አንድ ተቋም አገልግሎት ስሚፈልገው ዜጋ ተገልጋይ እንዴት ያየናል፤ከእኛ ምን ይፈስጋል፤ትኩረት የሚያደርገው ምን ሳይ ነው የሚሉ ጥያቄዎች ይዳሠሳሉ ፡፤በዚህ እይታ የዜጎችን ፍላጎት ለማሳካት የሚያስችሉ ደንበኞችን በአግባቡ ለማስተናገድና እርካታ መፍጠር እንዲሁም ተገልጋዩችን በድርጅቱ ደስተኛ እንዲሆኑ ማድረግን የሚያንጸባርቁ ግቦች ይቀረጻሉ ፡፡

የበጀት ;የፋይናንስ እይታ/ Finance budget Perspective/ በዚህ እይታ በጀት በሚመደብልን ውይም ፤የፋይናንስ ድጋፍ በሚያደርግልን አካል አይን እንዴት እንታይ የሚል ጥያቄ የሚመለስ ሲሆን በአግባቡ ስራ ሳይ የዋለ በጀት የቀነሰ ብክነት መጠን የመሳሰሉ ግቦች በእይታው ሲቀረጹ ይችሳሉ፡፡

የስራ ሂደት እይታ/ Internal Process Perspective/ በዚህ እይታ ዜጎች ተገልጋዩን ወይም በጀት የሚመደብልን መንግስት ፤ተልኳችንን ለመፈጸም ወይም እርካታ ለማስገኘት ፡በየትኞቹ

የሥራ ሂደቶችን ልቀን ብንገኝ ነው የሚደሰቱት የሚሉ ጥያቄዎቻችን የሚመልሱ ሲሆን የሚቀረጹ ግቦች የተቋምን አሰራር ሂደትና ዋና ዋና ተግባራት የሚመስከቱ ናቸው፡፡

የውስጥ እድገት እና የመማማር እይታ/Learning&growth Perspective/ በዚህ እይታ ራእያችንን እውን ለማድረግ ሠራተኞችን እንዴት ሲማሩ ሲግባቡና በጋራ ሲሰሩ ይችሳሉ? ሰራችን ቀልጣፋና ማድረግ የምንችለው ምን አይነት ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዘዴ ብንጠቀም ነው ? የመሳሳሉ ጥያቄዎች የሚመስሉ ሲሆን በዚህ እይታ ስር የሚቀረጹ ግቦች የአይምሮአዊና



ባለው ሰው ሃይል መጠቀም መቻል እንዳለባቸው በውይይቱ የጋራ መግባባት ሳይ ተደርሷል፡፡ ነገር ግን የሥራ ሂደቱ ጥናት ዘግይቶ የጀመሩት ፍርድ ቤቶች እናምርመራ ክስ የስራ ሂደት አሁን ጥሩ እንቅስቃሴ ቢደረግም ነገር ግን ሠራተኛው ሳይ የአመለካካት ለውጥ እንደሚያመጣ ሰፊ ስራ መስራት እንዳለበት የሴክተሩ ሃላፊዎች እና ስራ ሂደቱ አስተባባሪዎች አስተያየታቸውን ሰተዋል፡፡

ወንጀል መከላከል ስራን ለመስራት በዋነኛነት ህዝቡን ማስተማር እና በመከላከሉ ሳይ ክህዝቡ ጋር ውይይት በማድረግ የወንጀል መከላከሉ ስራ ተጠናክሮ ለመስራት ደሞ ፖሊስ ከህዝቡ ጋር በመሆን የኮሚኒዩቲ ፖሊስንግ ስራ ተጠናክሮ መሰረት መቻል አለበትእና በቀጣይ የኮሚኒዩቲ ፖሊሲንግ ስራ በቀጣይ የተጠናከረ ስራ መስራት አዳለባቸው የፖሊስ ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ አበራ አወል እንዳሉት ያሉት አባላት ቁጥቸው አናሳ ቢሆንም ነገር ግን

ባለው አባላችንም ቢሆን ከህ/ሰቡ ጋር ሆነው መስራት እንዳለባቸው ያሳሰቡ ሲሆን ነገር ግን አባላቱም በተመደቡበት ቀበሌ ከቀበሌ አመራሮች ጋር ቨመሆን ህዝቡን በማስተባበር ሁሉም አመራር ሲያግዛቸው እንደሚገባ አሳስበው በቀጣይ የወንጀል መከላከል ሳይ ትኩረት ተሰቶ መስራት መቻል እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙን ተግባራዊ በማድረግ ሁሉም ባለሙያ ሆነ



ሃፊዎች በዚህ ጉዳይ ሳይ የራሳችን ተነሳሽነት ያስፈልጋል እና ሞቅ ቀዝቀዝ ሳይሆን መሆን ያለበት ተጠናክሮ መቀጠል መቻል አለበት

# የሀላባ ልዩ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ለልዩ ወረዳው ፍትህ ሴክተር መ/ቤቶች ለአንድ ቀን የፓናል ውይይት አደረገ

የፓናል ውይይቱ ለአንድ ቀን የተካሄደ ሲሆን በውይይቱ የተገኙ አካላት፣ፍርድቤት፣ማረሚያቤቶች ተቋም፣ፍትህ ጽ/ቤት፣ፖሊ ሲሆኑ ሲክተሩ ሃላፊዎች የስራ ሂት አስተባባሪዎች የተገኙ ሲሆን ውይይቱ አጀንዳዎች የነበሩት:-

የመሰረታዊ የስ ሂደት ለውጥ እና አተገባበር

የፍትህ ስርአት ማሻሻያ እና የሲቪል ሰርቪ ሪፎርምን ያሰበት ደረጃ

የኮሚኒዩቲ ፖሊስንግ ያለበት ደረጃ

የመልካም አስተዳዳር መርሆችን ሁሉም አውቆ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር

በነዚህ በአራቱ አጀንዳዎች ላይ የልዩ ወረዳው አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሪት ሂክማ ከደረዲንና የፍትህ ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ አህምዲን መሃመድ ውይይቱን በመክፈት:- በልዩ ወረዳችን የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ወደ ሙሉ ትግበራ መግባታችን ይታወቃ::

በዚህ መሰረት ወደ ሙሉ ትግበራ በመግባት ለስራ ሂደቱ የሚያስፈልጉ የቢሮ አደረጃጀቶች ፣የሰው ሃይል ምደባ፣የማቴሪያል ዝግጅት በማድረግ ሙሉ ትግበራ ማድረጋችን ይታወቃል ሆኖም ግን በመጀመሪያ የሰው ሃይል ምደባ ሲደረግ እያንዳንዱ ሰራተኞች በማወዳደር እና በደንብ ቁጥር72/2001 መሰረት ሠራተኛው ውጤት ተሠፕቶ ከ50 በላይ ያመጡ ብቻ ምዳባ ተካሄዶ ድልድል በጥሩ ሁኔታ ተጠናቆ የጥናቱ ዶክመንት ባስቀመጠው መሰረት ወጪ፣ግዜን፣ጥራት፣ጠብቆ እየተከናወነ ነው፣የሚለውን በማንሳት ውይይት የተደረገ ሲሆን በማረሚያቤእና ፖሉስ የሙሉ ትግበራውን ቀደም ብለው የጀመሩ ቢሆንም ነገር ግን ስራ ሂደቱ ስሚለው በዶክመንቱ መሰረት ስራው እየተሰራ ቢሆንም የሚፈለገውን ደረጃ ላይ እየተከናወነ እና ሰው ሃይል እጥረት እንዳለባቸው ቢታወቅም



ድርጅታዊ ሀብት አጠቃቀምና የአቅም ግንባታ ስራዎችን እንዲሁም ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው::

## ባላንስድ ሶኮካርድ ከሌሎች አፈጻጸም ምዘና ማእቀፎች የሚለይባቸው ዋናዋና ነጥቦች

በተቋም ግቦች ስትራቴጂዎች መካከል ትስስር እንዲኖር ይረዳል

ተቋማት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮቻቸውን ሲመርጡ በተወሰኑ አቅጣጫዎች ይሰጣል

ቁልፍ የአፈጻጸም መሲኪያዎችን

ለማስቀመጥ ይረዳል

ከደንበኛ ጋር በቀጥታ የሚያገናኙ የሥ ሂደቶች ረገድ ትኩረት ለማድረግ ያስችላል

ግቦችን ለማሳካት ስትራቴያዊ እርምጃዎችን የአፈጻጸም ማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ ይረዳል

በተለያዩ ፈጻሚ ሃይሎች መካከል ውጤታማ ስራ ግንኙነት እንዲኖር ይረዳል

አፈጻጸምን በቀጣይነት ለመከታተል ለመመዘንና ለማሻሻል ያስችላል

በውጤት ላይ የተመሰረተ የሀብት አስተዳደር ስራ ለመዘርጋት ያስችላል

የተቋም ፣የቡድንና ፣የግለሰብ ፣ፈጻሚዎችን አፈጻጸም አስተሳስር ለማየት ያስላል

በአጠቃላይ አሁን በምንገኝበት አለም ተቋማት የማያጋጥማቸውን ምህረት የለሽ ውድድር እና ፈጣን ለውጥ ለመቋቋም እና በአሸናፊነት ለመወጣት አሰራራቸውን መለወጥ እና ተግባራዊነቱን የሚረዳ ዘመናዊ አፈጻጸም አመራር ስርአት መዘርጋት ግድ ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ገዚ የሆነው መርህ ለዘገች /ደንበኛጠቀሜታ

ያለው እሴት በመጨመር ዘላቂ የልማት ውጤት ማስመዝገብ ነው፡፤ ለዜጎች ወይም ለደንበኞች እሴት ለመፍጠር የተቋማት የሥራ ሂደት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን ማንኛውም ተቋም የተሳካ ውጤት ሲያስገኝ የሚያስችለው በተዋጣለት የሥ ሂደት አፈጻጸም ወስጥ ማለፍ ሲችል ነው፡፤

HUMAN RELATIONS

*THESIX MOST IMPORTANT WORDS

"Admit, I made amistake"author unknown

*THE FIVE MOST IMPORTANT WORDS

"You did good iob *

*THE FOUR MOST IMPORTANT WORDS

"What is your opinion?"

* THE THREE MOST IMPORTANT WORDS

"If you please"

* THE TWO MOST IMPORTANT WORDS

"Tank you"

* THE TWO MOST IMPORTANT WORDS

"We"

*THE LEAST IMOPRTANT WORDS

"I"

## የአመራር ቀዳሚ ተግባራት

ማቀድ

ማደራጀት

የቡድን አንድነት ማምጣት

የሠራተኞች እምቅ ችሎታ ማዳበር



ያስችላል፡፡

የሰው ሃይል እቅድ ዛሬ ያለውን የሰው ሃይል በቁጥና በሞያ ለይቶ ካስቀመጠ በሃላ ይህ ከሴክተሩ መዋቅርና የስራ እቅድ ጋር እንዲሁም የትኞቹ ሠራተኞች በጡረታ ወይም በሌላ ምክንያት የሚለቁበትን መረጃ በማገናዘብ ለምን የስራ መደብ ምን የሚያመች ተጨማሪ የሰው ሃይል እንደሚያስፈልግ ይተልማል፡፡ ከዚህ በመነሳሳት

ዝርዝር የቅጥር ፕሮግራሞች በማውጣት የሰው ሃይልፍለጋ መልምለንና ቅጥር በውቅቱ እየተካሄደ ተፈላጊ የሰው ሃይል በተፈለገው ግዜ እንዲገኝ ያደርጋል፡፤ በመሆኑም ሠራተኛ በዋናነት የሚመለመለው የሚቀመጠው ድንገት የስራ ክፍሎች ሲጠይቁ ሳይሆን በእቅድ ይሆናል፡፡ሰው ሃይል እቅድ ሲኖር ከት/ርት ተቋማትና ከቅጥር ወኪል ድርጅቶች ጋር በቅድሚያ ግንኙነት በማድግ ፍላጎትን ለማሳወቅ ተገቢውን ባለሙያ ለማግኘት ግዜ የሚሰጥ ይሆናል፡፤

ክፍት የሚሆኑ የስራ መደቦች ሁልግዜ ከውጭ የሚቀጠሩ ባለሙያዎች መሟላት የሚያስፈልጋቸው ሳይሆን ቅድሚያ ለሰጠው የሚገባው የድርጀቱ ሠራተኞችን ክፍት ሲሆኑ የሚችሉ የስራ መደቦች በስልጠና እያዘጋጁ መመደብ ነው፡፤ በመሆኑም ከውጭም ከውስጥም ሰለሚሟሉ የስራ መደቦች ነው የሚታቀደው በአዳዲስነቱ የሚቋቋሙ ድርጅቶች በማቋቋሚያ ጥናታቸው ወስጥ ሰው ሃይል ፍላጎት አካተው ሰው ሃይል ፈላጎታቸውን በወቅቱ መሟላት ያስፈልጋቸዋል፡፡

አንዳንድ ድርጅቶች በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ ወይም ስራ ማስፈት ፕሮጀክት ሲካሂድ የሌሎችም የማቋቋሚያና የማስፋፊያ ጉዳዩች ብዙ መቶ ሺ እና ከዛ በላይ ከወጡ በሃላ ሰው ሃይል ፍለጋ ይጀምራሉ ይህ አሰራር ኢንቨስትመንትን ልብክነት ይደርጋል፡፡ምክንያቱም ሠራተኛ በቶሎ ማግኘት ሰለማይቻል ኢንቨስት የተደረገው ከፍተኛ ገንዘብ እንደዚሁ ያለስራ ይቀመጣል፡፡

ለህሰ/ቡ በይበልጥ ለመቀየር ብቃት የማስፈጸም አውም ተብሎ ይገለጹታል፡፤ የማስፈጸም አቅም ባህሪይ ሶስትጣምራ ገጽታዎች አሉት፡፤

በይዘቱም ከገጽታዎች ማእከላዊ ስፍራ የሚይዘውን የሠለጠነ የሰው ሃይል ስራው የሚመራበትን ቀልጣፋና ውጤታማ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራርን ያካትታል፡፡

ሰው ሃይል ሲባል ሞያዊ እውቅና ክህሎት ያለው ስራ ስነ-ምግባር የተላበሰ የተሟላ ስብእናና አመለካካት እንደሁም ስራ ፈጣሪ ታታሪ የሆነ ዜጋን ያመለክታል፡፡ሌሎች ገጽታዎች ያሏቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር ስርአቶች ይዘት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

የማስፈጸም አቅም ልማት እቅዶችንበተግባር ሂደት ወስጥ በመመገብ እየገነባ ወደ ተጨባጭ ልማት የሚያደርስ አይነትኛ መሳሪያ ነው፡፤ በዚህ ሀገሪቱ የምትገኝበት ዝቅተኛ የማስፈጸም አቅም ደጃ ልማትን ለማረጋገጥ በተያዘው እንቅስቃሴ ወስጥ ዋነኛ ማነቆ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህም በተለያዩ የልማት ስትራቴጂ ሰነዶች የተመለከተ ሲሆን ከችግሩ መሰረታዊነት የጠነሳ ብሄራዊ የአቅም ግንባታ ስትራቴጂው ይህ ወሳኝ ችግ በአስተማማኝ ሀኔታ ለመፍታት ሲባል ተነድፏል፡

## የሰው ሃይል እቅድ

የሴክተሩ መዋቅር እና እያንዳንዱ የስራ ክፍል እቅዶችና የስራ ፕሮግራሞች መሰረት በማድረግ የሰው ሃይል ፍላጎት እቅድ ይዘጋል፡፤

ዚህ አይነቱ እቅድ ለማድረግ ያስሳል፡፡የስራ ትንተና በማኪካሄድበትና መዋቅር በሚዘጋጅበት ወይም እንዲሻሻል በሚደረግበት ግዜ ከዚህ ጋር የአሰራር ዘዴዎችች የተጠኑ ሰራዎችን የበለጠ ቀልጣፋ በሆነ ዘዴዎች እየተጠኑ ስራዎችን የበለጠ ቀልጣፋ በሆነ ዘዴ የሚከናወንበት መንገድ መፈለጉ የሰው ሃይልን ከሚፈለገው በላይ እንዲያሳልፍ ያስችላል፡፤ በመዋቅር ዝግጅት ግዜ ብቻ ሳይሆን በየግዜው የአሰራር ዘዴዎችንም መመርመር እና እንደ አስፈሳጊነቱ ማሻሻል የሰው ሃይል በተገቢው ቁጥር ለማቀድና ለመመደብ



ውጤት ተኮር ተግባራትን ማከናወን

ለውጥ ማራመድ ፤የተቋሙን ህ/ሰብ እስቶችን የማረምናእና አቅጣጫ ማስያዝ

ስራቸውን እንዲሰሩ የማነቃቃት ;የማትጋት ብሎም የማጎልበት

የግምገማ ውጤት ማሳወቅ

የበለጠ እንዲሻሻል መምከር ማሰልጠን ነው

የመምራት ዋና አላማ አሰራርን በማሻሻል ወደ ሚፈለገው ግብ ማድረስ በመሆኑ የሚጠበቀውን የሥራ ውጤትና በምን እንደሚለካ ማሳወቅንም ያጠቃልላል፡፡

### የመልካም አስተዳደር ምርሆች እና ዋነኛ ጽንሰ ሀሳብ

የመልካም አስተዳደር ማለት ግልጽኝነት ፤ተጠያቂነት፤ቀልጣፋ ውጤታማ አሰራር የህዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎ፤ዲሞክራሲ ፤የጋራ መንግስት ፤ፍትሃዊነት የህግ የበላይነት ፤የተረጋገጠበትና ለተያያዥ ነው ፈጣን አድገት ምቹ ሁኔታ የተፈጠረበት አስተዳዳር ማለት ነው፡፡

ይህ ተግባር እውን ሲሆን የሚችለው ደግሞ

በየደረጃው የሚገኙ የአመራርና አካልና ግንባር ቀደሞች ስለመልካም አስተዳዳር ጽንሱ ሀሳብና አተገባበር በቂ ግንዛቤ ናቸው፡፤በቀዳሚነት ሲተገብሩትና ሌሎችን እንዲተገብሩት ባልረቋረጠ ጥራት በተገቢው መንገድ ማስተባበርና መምራት ሲችሉ ብቻ ነው ፡፡ልዩ ወረዳው በየግዜው በሚያከናውነው የአሰራር ግምገማ በአመለካካት ፤በአደረጃጀት፤በአሰራር ላይ መሻሻል እያሳዩና ተቋማዊ የሆነ ለውጥ ለማምጣት መልካም ጅምር ላይ በመሆኑ ይታወቃል፡፤ከዚህ አንጻር በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችን በማሰልጠንና በተሳያዩ ስራ በማሰራት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፤ከመልካም አስተዳዳር ጋር በተያያዘ በአፈጻጻም የሚታዩ ችሮች ለመፍታት የወጡ ፖሊሲዎችን፤ፕሮግራሞችንና ፓጆችን ሳያቆራረጡ በአመራሩ በግንባር ቀደሞች በመንግስት ሰራተኞች በህዝቡ በራሱ በጋራ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ለማድረግ እና ለአምስተኛ ግዜ ቀጣይ የልማት አድገትን በማስመስገብ የድል ባለቤት ሆኖ የልዩ ወረዳው ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ነው ፡፡

ከዚህ አንጻር ቀድሞ ሲል ከህዝብ የተሰበሰቡ የመልካም አስተዳድር ችግሮች በቅርቡም የተለያዩ ጥራቶች እንዳረጋገጡት ጎልቶ ከሚታዩት ፍትሃዊነት፡፤የህግ በላይነት ፡፤በማረጋገጥ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ሆኖ ማስፈራራት ያለ አግባብ ማሰር እና መፍታት የመሳሰሉት የሚጠ ቀሱ ናቸው፡፤የተሳትፎና የጋራ መግባባት መርህን በመተግበር ረገድ የሚጣዩ ችግሮች ያሉ ሲሆን በግልም ሆነ በጋራ ልማት ስራዎች ሳይ የሚኖርን የህዝብ ተሳትፎ በፈቃድኝነት ሳይ የተመሰረተ አለማድረግ ደግሞ ከጉድለቶች ውስጥ ትልቁን ቦታ ሚይዝ ነው::

በተለይም በየደረጃው የሚገኙ ግንባር ቀደሞችና አመራሩ የላቀ የመሪነት ሚና/ድርሻ *ያላቸው መሆኑ ሊሰመርበት* የሚገባ ጉዳይ ነው፡፤በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ዙሪያ አመራሩ ግንባር ቀደሞች መወያት መከራከር ማቀድ መፈጸም ካልቻሉ ህዝቡን በየአካባቢው ልማት እንዲሳተፍ ማድረግ አይቻላቸውም::

በመሆኑም ህ/ሱቡ አገልግሎትን በፍጥነትና በጥራት እንያገኝ በግብአት ስርጭት በግብር አከፋፈል፡፤በፍትህ አገልግሎት በጸጥታ ጉዳይ ወ.ዘ.ተ የሚታዩ የመልካምአስተዳደር ችግሮችን በህግና በህግ አግባብ ብቻ ለመፍታት በግንባር ቀደሞች ተሳትፎ ማቃለል ተገቢ ይሆናል::

በየአካባቢው ያለው የመልካም አስተዳዳር ችግር የሚቃለለው በተደራጀ የግንባር ቀደሞች አመራር ሲረጋገጥ መሆኑም ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው፡፤ በመሆኑም የመሪነት ሚናቸውን በተገቢው ለመወጣትና ወደ ተግባር ለመሸጋገር ግንባር ቀደሞችና አመራር በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ሰነድ ሳይ መወያየት የሚጠበቅባቸው ሲሆን በየደረጃው ህዝቡን ማስተማር ማሰልጠን እና ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጦ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ማድረግ ይኖርባቸዋል::

በመልካም አስተዳድር ማለት፡- የህዝብን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ለፈጣን እድገት የተመቻቸ ሁኔታ የተፈጠረበት አስተዳድር ማለት ነው፡፤ሰለዚህ ሁሉም አመራር የመልካም አስተዳደር ስምንቱን መርሆችን ጠንቅቆ በማወቅ ሊተገብረው ጠንቅቆ ሊያውቀው ይገባል፡፤



አደረጃጀት እና ስርአት ሳይ ያተኩራል

እንዴት ብሎ ይጠይቃል

የአጭር ግዜ ዝረዝር እቅድና በጀት ይሰራል

በበሳይ አካል የሚመደቡ የመሾምነው

ሂደት ሳይ ይተኩራል

በእለት ተእለት ስራዎችና ባጭር ግዜ ግብ ሳይ ያተኩራል፡፤

ከሳይ እንደተሞከረው መምራት;መሪነት; ስራ መሪዎች በለውጥ ሂደት ወይም በተቋማዊ ለውጥ ወቅት ብቻ የሚያሳዩ ሲሆን ማኔጅመንት ግን ስራዎች/ሁኔታዎች/እንዳሉ ተገርተው በሚቀጥሉበት ግዜ የሚጠቀሙበት ተደርጎ ይወስድ ነበር ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑ እየጣወቀ የመጣና መሪዎች ጥሩ ማኔጀሮች፤ ማኔጀሮች ደግሞ ጥሩ መሪዎች ካልሆኑ ውጤታማ ሲሆኑ እንዳማይችሉ በተግባር ተስተውሏል::

በመሆኑም ውጤታማ ማኔጀር ለመሆን የሚያስፈልጉ ክህሎቶች ሁሉ ውጤታማ መሪ ለመሆንምየሚያስፈልጉና ውጤታማ መሪ ለመሆንም የውጤታማ ማኔጀር ክህሎቶች ሰለሚያስፈልጉና መረነትና ማኔጀር ተነጣጥለው የሚታዩ ሳይሆን ተደጋጋፊ ናቸው፡፤

‹‹የስራ መሪዎች እንዴት ማስተዳዳር እና መምራት እንዳለባቸው በሚገባ ሊያወቁ ይገባል::››

## የማስፈጸም አቅም ብሔራዊና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ

የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታእና ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት የአንድን አገር ቀጣይ ህልውና የህ/ሰቡን ሁለንተናዊ በልጽገና ለማረጋገጥ አብይ መሰረቶች ናቸው፡፤ ለዚህ ጥረት ስኬት ደግሞ ተጨባጭ ውጤት አምጪ የሆኑ የልማትን ግቦችን መቅረጽና መተገበር ይጠይቃል::

ይህ ልማት ግቦችን የመቅረጽ የተፈጥሮ ሀብትና ማህበራዊ ግንኙነትን

# መሪ

አዲስ አሰራርና ፈጠራን ያበረታታል

ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት ይጥራል

ሰራተኞች እንዲበቁ ያነሳሳል

ለረጅም ግዜ ራእይ ይሰራል

ትብጥር ያበረታታል

አሰራሮችን የሚያሳድግና የሚለውጥ ነው

ሰው ላይ ያተኩራል

ምን እና ለምን ብሎ ይጠይቃል

የረጅም ግዜ ራእይ ይነድፋል

ከራሱ በመነጩ ተነሳሽነት  ይመራል

ውጤት ላይ ያተኩራል

የተቋሙ የረጀም ግዜ ራእይና አላማ ላይ ይተኩራል፡

# ማኔጅር

ነገሮችንበተለመደው አሰራር እንዲቀንሱ ይፈልጋል

ስትራቴጆዎችንና ፕሮግራሞችን ይቀርጻል ይተገብራል

ስራን ያከፋፍላል ይቆጣጠራል

ለአጭር ግዜ ግብ ይሰራል

ወጥነት / አንዳዊነትን/ያጠናክራል

አሰራሮችን ከነባሩ አካሄድ ፈለግ እንዳይወጡ ይጠብቃል



**ተሳትፎአዊነት**፡- ማለት የሚመለከታቸው ወገኖች በአንድ አላማ ወይም እቅድ ላይ ከሀሳብ ጀምሮ አስከ ተግባሩ በሚገባ የተሳተፈበት ማለት ሲሆን በዚህ መልኩ የሚፈጠር አሰራር እቅድ የተሳካ ይሆናል ወይም የሚሆን እድሉ ከፍተኘሠ ነው፡፡ ሰለዚህ ህ.ሱቡን ነዋሪው ህዝብ አርሶ አደሩና ሠራተኛው ወ.ዘ.ተ) የእቅድ ሀሳብ በማመንጨት የእቅድ ቅድመ ተከተል በማውጣትና በመወሰን ግንባታ ወይም ልማት ወ.ዘ.ተ.የሚከናወንበት ቦታ በመምረጥ እና በመወሰን ግንባታ ወይም ልማት ወ.ዘ.ተ የሚከናወንበት ቦታ ለመምረጥ እና ለመወስን በበጀት ድልድል አመዳደብና አጠቃቀም በተግባራዊ እንቅስቃሴው ስራውን መከታተል፤ ውጤቱን መገምገም እና የተሸለ አቅጣጫ መጠቆም ወ.ዘ.ተ መሳተፍ እንዲችል ማድረግ የተሳትፎአዊነት መግለጫ ነው፡፤ስለዚህ በማንኛውም ተግባር ህዝቡን መሳተፍ ተገቢና ቀዳሚ ተግባር ይሆናል፡፡

**የጋራ መግባባት**፡- ማለት በራእይ ላይ፤በግብላይ፤ በመርህ ላይ፤በእቅድላይ በመመሪያ ላይ የጋራ አመለከከት መያዝ ማለት ነው፡፡ይህም ለጋራ ጎዞ የጋራ መነሻ የሆነ ሃይልና አቅም የሚሰጥ ነው፡፡

ለሚፈለገው ራእይ መርህ እቅድና አፈጻጸም ላይ የጋራ መግባባት ሲኖር ፈተናዎችንና ችግሮችን ሁሉ በጋራና በቆራጥነት መወጣትና ለስኬት መብቃት ያስችላል፡፡ሰለሆነም ለህዝቡ ይተቅመሀል ብለን በምናቀርብለት ተግባራት ሁሉ በማሳወን የጋራ መግባባት ፈጥረን መሰራት ይጠበቅብናል፡፡

**ቶሎ ምላሽ መስጠት :-** ማለት ለሚመለከታቸው ወገኖች ተጨባጭ ችግር መጨነቅና ምላሽ መስጠት መቻል ማት ነው፡፡ ወቅታዊ ምላሽ የችግር አንሺዎችን ችግር በጸሞና ሰምቶ በሚገባ ከመገንዘብ ጀምሮ ወዲያው መፍትሄ ሲሰጥ ያልቻለበትን ምክንያት አስከ ማስረዳት ማሳወቅ እና በዚህም ላይ አስከ መግባባት የሚዘልቅ ተግባር ነው፡፤የሚቀርበውን ችግር በሚገባ መሰማት መረዳትና ፤መጨነቅ የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን

ሲፈታ የሚችል ከሆነ ወዲያው መፍታት ካልቻለ የማይቻልበትን ሁኔታ ማስረዳትና መግባባት ላይ መድረስ ማለት ነው፡፡

4.ግልጽነት፧-ሲባል ህዝቡ በመንግስት ፖሊሲዎች፧እቅዶች፧በመመሪያዎች እና ተግባራት ላይ ሁልግዜ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ ማት ነው፧ ግልጽነት፧የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ምን እንደሚመስል በምን መርህናህግ እንደሚመራ እንዴት እንዲፈጸም ፧በማን እንደሚፈጸም ወ.ዘ.ተ ማለት ነው፡፡ ህዝቡ ደግሞ ሀላፊዎችን ነውየቀጠረን፧የመረጠን ስልጣን የሰጠን ህዝቡ ነው፧ ለሃላፊዎችን ለቀጠረንና ለመረጠን ስልጣን ለሰጠን ህዝቡ የምንደብቀው ነገር ሊኖር አይገባምና፡፡

5. ተጠያቂነት፧- እያንዳንዱ ሰውና አካል በስራውና በውጤት ተለክቶ ጥሩ ስራ ሲሰራ የሚበረታታበት ጥሩ ስ ሳይሰራ ሲቀር የሚስተካከልበት ወንጀል ስራ ሲሰራ ደግሞ የሚቀጣበት ስርአት ማት ነው፡፡ ሁሉንም የልማትና የማህበራዊ ጉዳይ ስራዎች ግልጽ ማድረግ ትክክለኛ መረጃ መያዝና ስህተት ከተፈጠረበት ማረምና የተጠያቂነት መርህ ተግባራዊ ማድረግ ይጠቀብለናል ፡፧ግልጽነት ተጠያቂነት ተደግፈው የሚሀዱ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳዳር መርሆች ናቸው፡፧

ፍትሃዊነት፡-( እኩል ተጠያቂነት፡- ማለት አድልኦ እና በደል አለመፈጸም ከመሆኖም በላይ ሲጎዱ የሚችሉ ወገኖች በግልጽነት መርህ ቢታወቁ መስፍቶች እንዳይጎዱ ወደ ሃላ እንዳቀሩ መከላከል ማት ጭምር ነው፡ልናደርግ የሚገባን ተግባር ለምንደርግለት ህዝቡ ሁሉ ( ድሃ፧ሀብታም፧ደካማ ፧ጉልበተኛ፧ሴት፧ወንድ፧ልጅ፧አዋቂ ፧አመራር፧ተሻሚ፧ተራ ዜጋ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መፈጸም አለብን፡፡

7. የህግ የበላይነት፡- ማት ሁሉም ዜጎችምቶችና ጥቅሞች በእኩልነት የሚጠበቁበት የዲሚኮራሲ ስአት መሰረት የሆነ መርህ ነው፡፡ባለስልጣኑ ፧ሀብታም፧ጉልበተኛ፧ከተራው ዜጋ ከድሃውና ደካማው ጋር በህግ ፊት እኩል የሚታዩበት ( የሚዳኙበት) መርህ ነው፡ በመሆኑም የህግ የበላይነት መርህ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳዳር ምሶሶ ነው፧ እኛም የምንፈጽመው በህግና በህግ አግባብ ብቻ ሲሆን ይገባል፡፡





## የመሪነት ክህሎት ምንድ ናቸው?

1.መሪነት ሰዎች ወደ አንድ የጋራ አላማ እነድሰለፉ የማነሳሳት እና እምነት የመፍጠር ችሎታ ነው፡፡

2.መሪነት ሰዎችን የማግባባት ችሎታ ነው

3.መሪነት ሰዎችን የማነሳሳት የማቃቃት የማንቀሳቀስ ነው፡፧

ብዙ የመሪነት መጽሃፍት የመሪነት ክህሎቶችን ጽንስ ሃሳብ በተለያዩ አቀራረብ እና መጠን ሲያቀርቡ ይጣያል ፡፡ሰለሆነም ጸሃፊ ሄርሳይ እና ብላንቻርድ (19-88) እንጻፉት ብዙ የተለያዩ የመሪነት ክህሎቶች ቢኖረውም ዋናዋናዎቹ ዋሳኞቹ ከዚህ የሚከተሉት መሆናቸውን በመጻፋቸው ገልጸዋል፡፡

1.ቴክኒካዊ ክህሎት/Technical

2.ሰብአዊ ግንኙነት / Human Relation skills/

- የግንኙነት ሚና / Communicati -

ማትጋት / Motivation/

3.ንድፍ ሃሳባዊ ክህሎት /conceptual skills/

- ውሳኔ መስጠት/ Decision making
- የስልጣን ውክልና /Delegation/
- የሥራ ቡድኖች ምሰረታ/ team building/

መሪ በመሆንና ማኔጀር በመሆን መካከል ያለውን ሚና/ተግባር እንዳንድ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

ነበር፡፤ደካማዋ እናቴ በድህነት አልጋዋ ላይ ተኝታለች፡፡አርጅናና በሽታ ተዳምሮ እናቴ በጣም ተዳክማ ነበር፡፤ትኩር ብላ አየችኝ፡፡ከህመሟጋር ታግላ ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡እኔን እንዳይከፋኝ የምታደርገውነገር እውነኛና ከልብ የመነጨ ስሜቷን ይገልጽ ስለነበር አፍጥጬ እያየሃት እምባዬ ይወርድ ነበር፡፡እናቴን በዚያሁኔታ ስላገኝኋት በጣም አዘንኩ ፡፤ያቺ ብርቱና ጠንካራዋ እናቴ አቅም አንሷታል፡፤ቢሆንም ለኔ ማለት የምትፈልገገውን ለመግለጽ የሚሆን አቅም አላጣችም፡፡ከህመሟይልቅ የኔ ሁኔታ ነበር ያሳሰባት የኔ ወድ በቃ አታልቅስ አያመኝም ይህን ካለችኝ በሃላ እናቴ አይኗን ለዘለአለሙ ጨፈነች፡፡

## የመሪነት ክህሎት / Leader ship skills /

ያለ ብልህ አመራር አገልግሎትን ለማሻሻል ለማቀላጠፍ አይቻልም፡፡በክልላችን ብሎም በልዩ ወረዳችን ፋጣን እድገት በሁሉም ዘርፎች ለማስመስገብ ብቃት ለው አመራር ያስፈልጋል፡፤ይህንን ሁኔታ ለማሳካት የመሪ ት/ርቶችን እና ስልጠናዎች እየተሰጡ ናቸው፡፡በልዩ ወረዳው አቅም ግንባታ ሴክተር ወቅቱ የሚጠይቅውን የመሪነት ክህሎት/ Leader ship skills/ ለማስጨበጥ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ሰለሁነም የዚህ ጹሁፍ ዋና አለማ በመሪነት ስራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ የስራ ሃላፊዎች የመሪነት ክህሎትን ለማጎልበት የሚደረገውን ጥረት ለማስመዝገብ ነው፡፡

የመሪነት ክህሎቶችን ከማየታችን በፊት በቅድሚያ

መሪነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡

*መሪነት በየትኛውም መልኩ የተቀየሱ አላማዎች የታለመላቸውን ግቦች እንዲመቱ ቡድኖችንና ሠራተኞችን በማሳንና በማግባባት እንደሁም በመደገፍ ከትግባራዊ ነታቸውንና በመሉ ልብና በቁርጠኝነት እንዲቀሳቀሱ ለማድረግ እና ውጤት የማስገኘት ችሎታ ሲሆን በተለያዩ ምሁራን ሲተሮገም



8.ቀልጣፋና ውጤታማነት፡-ቀልጣፋነት በፍጥነት ተገቢውን ሀብት (ገንዘብ፤ጉልበት፤ቁሳቁስ፤ግዜ፤ ተጠቅሞ መስራት የሚያመለክት ሲሆን ውጤታማነት ደግሞ በተደረገው ቅልጥፍና ስራ የሚፈለገውን ለውጥ መምጣቱ የሚያመለክተው ነው፡፡ ቀልጣፋና ውጤታማነት የመልካም አስተዳደር ሌሎች ከላይ የተገለጹት ሰባት መርሆ የሚቋጭበት ነው፡፡

## የኢትዩጵ የሲቪል ሰርቪስ ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ የሲቪል ስርቪስ ረጅም አመታት ያስቆጠረ ቢሆንም በተለያዩ አሰራር፤በአመለካከት፤በአደረጃጃት፤ችግሮች ተተብትቦ የቆየ በመሆኑ አገሪቱ መልካም አስተዳዳርን ለማስፈን ፤ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባትና ልማት ለማረጋገጥ በምታደርገው ትግል ወስጥ የሚጠበቅበትን

ቁልፍ ድርሻ ባለመወጣቱ የተገልጋዩን ህ./ቡን ፍላጎት ለማርካት አለመቻሉ በተጨማሪ ፡-

የህዝብ አገልጋይነት አመለካካት አለመዳበር

ተገልጋይ ተኮር አለመሆን

ለተገልጋይ መብት እውቅና አለመስጠት

ተገልጋይ አለማማከር

የማኔጅምንት ሃላቀርነት

የአሰራር ግልጽነት አለመኖር

የተጠያቂነት መርህ አለመዳበር

የተንዛዛ አደረጃጀት እና የሥራ ክፍል እና የሚያቶር አደረጃጀት ፍልስፍና መሰረት ያደረገ በመሆኑ ባለንበት ዘመን ግሎባላይዜሽን ከሚጠየቀው አንጻር የሲቪል ስቪሱና ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ሳይችል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ዘመኑ በሚጠይቀው የተገልጋይ ፍላጎት መሰረት ያደረገ አሰራር መኖር የግድ ይላል፡፡

*መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የሰራተኞች የድልድል መስፈርት ሁሉም ተገንዝቦት ይሆን?

1.የትር/ት ዝግጅት 17%

2.የውጤት ተኮር እቅድ ዝግጅት አፈጻጸም 16%

3.የሥራ ልምድ 12%

4.የማህደር ጥራት 5%

5. ለለውጥ ያለው ተነሳሽነት 18%

6.መልካም አስተዳዳር 14%

7.አገልግሎት አሰጣጥ 18%

ከላይ የተረዘሩትን መስፈርቶች በመሰረታዊ የስራ ሂደት በየጽ/ቱ የድልድል ኮሚቴ ውጤቶች ከተሞሉ በሃላ ከ50% በላይ ያመጣ ሠራተኞች በተወዳዳሩበት ቦታ በየደረጃው ቦታ የሚይዝ የሚመደብ ሲሆን ነገር ግን የተዘረዘሩት መስፈርቶች ውጤት 50% በታች ማትም 49.9 ቢያመጣ እንኳን መመደብ የማይችል መሆኑን ሁሉም ሊያውቁ ይገባል::

የስነ ምግባር መርሆች

## የስነ ምግባር መርሆች

## ተስፋ አስቆራጭ አባባሎች / Killer phrases/

*ተስፋ አስቆራጭ አባባሎች ባለን በዚህ ጹሁፍ የምናያቸው ሲሰራ አካባቢ የውጭና የወስጥ ተገልጋዩች ከስራ ክፍሎች አገልግሎት ለማግኘት በሚያደርጉት ሂደት ተዘውትረው የሚመደቡ አባሎችን ነው:: እንዚህ አባባሎች በግልም ሆነ መንግስት ተቋም የሚሰጡ አገልግሎትንች በማጓተት እና በመገንዘብ የተገልጋዩን የሰራተኛውን ስራ ተነሳሽነት የሚያዳክሙ እና ጌዜንና ገንዘብ የሚያባክኑ በአጠቃላይ ቀልፋና ውጤታማ ስራ እንዳይሰራ የሚያደርጉ ናቸው:: ጥቂቶችን እንመልክት :-

መመሪያ አይፈቀድም

በጀት የለም

የሰው ሃይል የለንም



ቢሆንም እኔን ለማሳደግና ለቁም ነገር ለማብቃት ያላት ብቸኛ አማራጭ ይህ ነበር::ችግሩ በሷ አቅም ብቻ የሚፈታ አልነበረም::ከግዜ ወደ ግዜ ችግሩና መከራው እየበረታ መጣ፡፤እኛም መጋፈጡን ቀጠልንበት::ከጎረቤታችን የሚኖረው አጎታችን ሁሌም በችግሮቻችን ከጎናችን ነበር::ሌላው ጎረቤታችን ግን እድለኛ እንዳልሆንን በመግለጽ እናቴ ባል እንድታገባ ይመክራት ነበር::ለዚህ ሰው ምክር እናቴ ቁብ አልሰጠችውም::ብታገባ የኑሮ ጫናው በመጠኑም ቢሆን ይቀንስ እንደነበር አሳጣችምውም ነገር ግን ምላሻ እኔ ማግባት አልፈልግም የሚል ሆነ::ይህ አምስተኛ ውሸቷ ነበር::

ትምህርቴን አጠናቅቄ ከተመረቅሁ በሃላ ሥራ ያዝኩ፡፤ይህግዜ ለኔ ስትል መከራ ያየችሁ ደካማዋን እናቴን የምረዳበትና የምጦርበት ግዜ ነው ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ ፡፤ነገር ግን እናንተ የኔን መጦር አልፈለገችም፡፤እኔ ከምሰጣት ገንዘብ ይበልጥ ያስደስታት የነበረውን በየቀኑ ጧት ወደ ገልት ገበያ እየሄደች አትክልት በመሸጥ የምታገኘው ገቢ ነበር:: በዚህም በመጠኑም ቢሆን የሚያሰፈልጋትን ማሟላጽ ጀመረች::

እኔ በሥራ ምክንያት ከሷ ርቄ ለለምኖር ለሚያሰፈልጋት ወጪ እንድትጠቀም በየጊዜው የምልክላትን ገንዘብ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረችም:: ይባሰ ብላ የምልክላትን ገንዘብ መልሳ ትልክልኝ ነበር:: ለምን በገንዘቡ አትጠቀሚም ? ሰላት እኔ በቂ ገንዘብ አለኝ ያንተን አልፈልግም ትለኝ ነበር:: ሰድሰተኛው ውሸቷ ነበር::

በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቄ ሥራ ከያዝኩ በኃላ ወደ ትምህርት በመመለሰ ሁለተኛ ዲግሪዬን አንድ ኩባንያ በሰጠኝ የነፃ ትምህረት እድል ቀጠልኩ:: ትምህርቴን ሳጠናቅቅ የትምህርት ወጪዬን በሸፈነልኝ ኩባንያ ውሰጥ ተቀጥሬ መሰራት ጀመርኩ::

የሚከፈለኝ ደመወዝ ክፍተኛ ሰለነበር እናቴን እኔ ጋ በማምጣት ቀሪ ህይወቷን በደሰታ እንድታሳልፍ ወሰንኩ:: ውዷ እናቴ እኔን ያሰቸገረች መሰሏት ያልለመድኩበት አልሄድም የሚል ምክንያት በማቅረብ እምቢታዋን ገለፀች:: ውሸት ሰባት መሆኑ ነው::

እናቴ ዕድሜዋ እየገፋ ሲሄድ በካንሰር ህመምተያዘችና ለሆስፒታል አልጋ ተዳረገች::በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቄ ከምኖርበት እናቴን ሳሳክማትና ልጎበኛት መጣሁ፡፤እናተን ያገኘሃት በጣም ከስታ ተጎሳቁላና የቀዶ ህክምና አድርጋ ወደ ቤቷ እንደተመለሰች

ይጨምራል፡፡እኔ ዓሳውንእየተመገብኩ እናቴ ከአጠገቤ ቁጭ ትልና እኔ በልቼ በጣልኩት የዓሳ አጥንት ሳይ የተራረፉ ስጋዎችን መለቃቀም ትጀምራለች ፡፡የእናቴን ሁኔታ ሳይ ልቤ በጣም ስለሚነካ ከቀረበልኝ ሳይ ብይው ብዬ ስሰጣት ፈቃደኛ አትሆንም፡፤የምትሰጠኝ ምላሽ የሚገርም ነበር ልጄ ብላው ዓሳ መብላት አልወድም ፡፡ይህ ሁለተኛው ውሸቷ ነበር፡፡

አድጌ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትተማሪ ሆኛለሁ፡፡ ኑሮአችን ምንም መሻሻል አይታይበትም፡፡ኑሮአችንን ለማቃናት እናቴ ቀን ከሲሴት ደፋ ቀና ማለቷግን አልቀረም ጠብ የሚል ባይሆንም፡፡እናም እናቴ አንድ የንግድ ተቋም አገልግሎት የሰጡ የክብሪት ፓኮዎች ከሚጣልበት እየሰበሰበች መሸጥ ጀመረች ፡፡ይህን የምታደርገው ኑሮአችንን ለመደጎምነበር፡፡አንድ ሌሊት ከእንቅልፌ ስነቃ ጭልጭል በምትል የሻማብርሃን ታግዛ የሰበሰበቻቸውን ያገለገሉ የክብሪት ፓኮዎችንለሽያጭ ስታሰናዳ አገኘኋት፡፤ደንግጬ እማዬ ለምን አትተኝም እኩለ ለሌት አልፏል፡፤ነገ ጧትስለምትሄጂ ይደክመሻል አልኳት እናቴ ፈገግ በማለት ድካማን እየደበቀች የኔ ወድ ተኛ እኔን አልደከመኝም አለችኝ፡፡ሦስተኛው ውሸቷነበር

የዐመቱን የትምህርት ግዜ አተናቅቂ ፈተና የተቀመጥኩበት ግዜ ነበር፡፤እናቴ ከስራ እረፍት ጠይቃ እኔን ለመቀበል ወደ ትምህርት ቤት መጣች፡፤የጸሃዩን ቃጠሎ ለመቋቋም

የማይቻልናእጅግ ሀይለኛ ነበር፡፤ለእናቴ ግን ይህ ምንም አልነበረም ሀይለኛውን የጸሃይ ንዳድ ተቋቁማ ምንም ጥላ በሌለበት የመጨረሻው የፈተናውን ክፍል እንደወጣው እናቴ አንድ ነገር ሸጉጣ እየጠበቀች መሆኑን አየሁ፡፡ይዛልኝ የመጣችሁ ከከንፈር አልፎ ጉሮሮን የሚያደርቀውን የጸሃይ ንዳድ ለመቋቋም የሚያስችል ሻይ ነበር ፡፤ቀድታ ሰጠችኝ፡፤ እናቴ ለእኔ ስትል አያየች ያለውን መከራ አስተዋልኩ፡፤ጥንካሬዋንና ጽናቷን በውስጤ እያደነቅሁ እንደኔው የደረቀውን ጎሮሮዋን እንድታርስ ከሻዩ እንድትጠጣ ጠየካቋት ፡፡እናቴ ግን ልጄ ጠጣውእኔ አልጠማኝምአለችኝ፡፡ወሸት አራት አልኩ፡፡

ወላጅ አባቴ በህመም ከሞተ በሃላ እናቴ ለሁለት ይወጡት የነበረውን ሃፊነት ለብቻዋ መጋፈጥጀመረች፡፡ለሁለት ያልቻሉትን ለብቻዋ ለመወጣት ጥረት ማድረጓምን ያህል ጫንቃዋን እንደሚያጎብጠው አላጣሁም፡፡



ነው ግን ---

አይሰራም  እኛም ሞክረ ነው ያቀተን ነው

እኛ እንደሌሎቹ አይደለንም

እኛ ጋ ለውጥ የሚፈልግ የለም

ማስታወሻ አቅርብ

እንዲህ ነው ስንሰራ የኖርነው ልንለውጠው  አንችለው

የስራ ድሻህ አይደለም

አይቻልም !

ኮሚቴ አልተበሰበም

ሃላፊው የልም

ሀሳብ ትክክል ነው በተግባር ግን ልንፈጽም አንችልም

አይመለከተኝም - - - - ወ.ዘ.ተ

እነዚህ መሰል አባባሎች በአዲሱ መሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ አገልሎት መስጫ ክፍሎች ወይም ከስራ አካባባ መወገድ አለባቸው፡፡

1.ተሳትፎአዊነት

2.የጋራ መግባባት

3.ቶሎ ምላሽ መስጠት

4.ግልጽነት

5.ተጠያቂነት

6. ፍትሃዊነት

7.የህግ የበላይነት

8.ቀልጣፋና ውጤታማት

## የስነ ምግባር መርሆች እና የመልካም አስተዳዳር መርሆች ልዩነታቸው በግልጽ ይታወቅ

የስነ ምግባር መርሆች እና የመልካም አስተዳዳር መርሆች ልዩነታቸው በግልጽ ይታወቅ

1.ሀቀኝነት

2.ታማኝነት

3.ግልጸኝነት

4.ሚስጥር ጠባቂነት

5.ቅንነት

6.ተጠያቂነት

7.የህዝብ ጥቅም ማስጠበቅ

8.ስልጣን በአግባቡ መጠቀም

9.አለማዳላት

10.ህግን ማክበር

11.ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት

12.አርያ መሆን

እነዚህን የመልካም አስተዳዳር መርሆች እና የስነ መግባር መርሆችን በደንብ በመገንዘብ ሆነ ሠራተኛው በጥንቃቄ ሲፈጽመው ይገባል።

በአጠቃላይ የለውጡን ሂደት በሚፈለገው መልኩ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ግምገማ ሰነድ በማዘጋጀት ስራ ሂደቱ ሲመተገበርባቸው ሴክተሮች በመዘዋወር ቢታዩ ክፍተቶአ እና የተሸሉ አፈጻጻሞች ሳይ የየሴክተር ሃላፊዎችና የስራ ሂደት አስተባባሪዎች ስብሰባ በመጥራት እና የየሴክተሩ አፈጻጻም እና ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይቶ ሲቀመጥ የልዩ ወረዳው ዋና አሰተዳዳር እና ልዩ

ወረዳው አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ሃላፊ ያሉ ጠንካራ ጎኖች ሌሎችም ተሞክሮ በመሆን ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት እና ለውጡን መተግበር ደረጃ ወደ ሃላ የቀሩና ሴክተሮችን በቀጣይ ያሉ ክፍተቶች እያሻሻሉ መሄድ እንዳለባቸው እና አሮጌው አሰራሮችንና አስተሳሰቦችን በአዲስ መተካታቸውነን ስራ ሂደቱ በተጠናው መሰረት ተግባራዊ መሆን መቻል እንዳለበት እና ሃላፊዎች እና የስራ ሂደት አስተባባሪዎች በተጠናው መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ተደራሽ ግቦች መሳካታቸውንና ለተገልጋይ እርካታ የሰገኙ መሆኑን ለለውጡ በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት መተግበሩንና እና ሳጋጠሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ



በመዘዋወር ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት የተደረጉ ዝግጅቶች ሃላፊዎችና ሰራተኞች በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ስልጠና መወሰዳቸው ፤ስራ ሂደት ባለቤትና አስተባባሪዎች ሰው ሃይል መመደቡንና የቢሮና የመሰረታዊ ቦታ ዝግጅት ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች መሟላታቸውን በስራ ሂደቶች መካከል ሰለሚኖር ግንኙነት የሃላፊዎችና የአስፈጻሚዎችሚና የስራ ሂደት አስተባባሪ በስራቸው ካሉ ሰራተኞች ጋር ያላቸው የስራ እንቅስቃሴ እና ሊለወጡ ያላቸው ተነሳሽነት፤ ንዲሁም

አገልግሎትን ለማፋጠን የየስራ ሂደታቸውን እንቅስቃሴ የየእለቱን እገመገሙ ስለመሆናቸው እና የጥናቱ ድክመት በተቀመጠው ስንታንዳርድ መሰረት ተግበራ እያከናወኑ መሆናቸውን እንዲሁም ሁሉንም ባለጉዳይ በግልጽነት፤በመግባባት፤ቶሎምላሽ በመስጠት፤በፍትሃዊነት እያገለገሉ መሆናቸውን ለባለጉዳይ አገልግሎት ለማፋጠን እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም የበላጉዳይ እርካታ በአገልሎት መደሰቱን እና ቅሬታ ካው በየስራ ሂደቱን

የአስተያየት መስጫ ፎርማቶች ተዘጋጅተው እየተተገበሩ መሆኑን እንዲሁም ባጉዳይና ሠራተኞች ተለይተው የሚታወቁበትን የሠረተኛው የደረት ባጅ:ዩኒፎም እየተጠቀሙ --- - - - መሆናቸውን ::

## ስምንቱ የእናቴ ‹‹ ውሸቶች›.

የእናቴ ‹ውሸት› የሚጀመረው ከልጅነት ግዜዬ አንስቶ ነው። ጠግበን መብላት የማንችል ስለነበርን ከድሃ ቤተሰብ የተወለዱኩኝ ነኝ› ማቴ ብቻ የኑሮአችንን ሁኔታ ለመግለጽ ጉልበት ያንሰዋል።የምግብ ሰአት ሲደርስ እናቴ ሁልግዜ የምታደርግልኝ ነገር አይሳምሳኝም፡፤ ለምግብነት የሚቀርብልን ሩዝ ነበር።

እናቴ ታዲያ የድርሻዋን ሩዝ ወደ እኔ መመገቢያ ዕቃ በሙሉ ትገለብጥና ይህንን ጨምረህ ብላው የኔ ልጅእኔ አልራበኝም ትለኝለች።እንዳልበላችና እንደሚርባት እያወቁሁ የምትለኝን ሁሉ እቀበላለሁ፡፤ይህ የእናቴ ውሸት የመጀመሪያ ነው።

እያደግሁና ልቤ እያወቀ ሲሄድ እናቴ ከሥራ እረፍት በሆነች ግዜ ከቤታቸችን አቅራቢያ ከሚገኘው የዓሳ ማጥመጃ ኩሬ ዓሳ ታጠምዳለች፡፤ይህን የምታደርገው ዓሳን መመገብ ጤናማና ለተሟላ ዕድገት ጠቃሚ መሆኑን ስለተረዳችነው፡፤ ስለዚህም ትኩስ የዓሣሾርባ

ትሰጠኛለች።ዓሳውን መመገቤም የምግብ ፍላጎቴን

## ወደ ሙሉ ትግበራ ለገቡ ሴክተር መ/ቤቶች በመስክ ጉብኝት ሞያዊ ድጋፍ ተሰጠ

የሙሉ ትግበራ ስራን ይበልጥ በቅርበትና ስርአት ባው መልኩ ለመከታተል እንዲሁም ቤሴክተሩ ሲፈጸሙ የሚገባውን ስራ በትክክል ተከናውኖ የተጠናቀቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የልዩ ወረዳው የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ስትሪንግ ኮሜቴ ሙሉ ትግበራው የሚከናወኑባቸው እና የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በቅድሚያ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሴክተሮች

ከልዩ ወረዳው፤- 1. አቅም ግንባታ

2.ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት

3..ግ/ገ/ልማት ጽ/ቤት

4. ፍትህና ጸጥታ

5. ፖሊስ ጽ/ቤት

6.ማረሚያ ተቋም

7. ት/ርት ቤቶች ጽ/ቤት

ከከተማ አስተዳደር 1. ንግድና ኢንድስትሪ

2. ማዘጋጃ ቤት

3. ፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት

4.ፖሊስ ጽ/ቤት





በመስጠት ለውጡ ሞቅ ቀዝቀዝ ሳይል ሁሉሃላፊዎች እና የስራ ሂደቱ አስተባባሪዎች ለዚህ ለውጡ ትልቅ ሚና ስለሚጫወቱ ለውጡን እንዳይቀለበስ የበኩላቸውን አስተዋእጾ በማድር ለውጡን መተግበር መቻል አለባቸው፡፡

### የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ማለት

- አሮጌውን አስወግዶ በአዲስ መተካት
- እንደገና አዲ መጀመር
- ነባሩን ሰነድ ትቶ አዲስ ሰነድ መስራት
- አዲስ መፍጠር
- አሮጌውን ታሳቢዎች ውድቅ በማድረግ
- የእንዱስትሪው አባዎት የወለደውን አዳም ስሚዝ የስራ አደረጃጃት አስተሳሰብ የነበረውን ታማንነት በመጣስ አዲ ስራ አደረጃጀት ሞዴል መትከል ነው፡፡

ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሁላችንም
በጋራ እንስራ !!